# የተበደለ፣ የተጎሳቆለ፣ እና የተተወ/ትኩረት የተነፈገው ልጅ ማጤን እና ሪፖርት ማድረግ
## ለበጎ-ፈቃደኞነት ዘወትር የሚቀርቡ ጥያቄዎች

(MCPS) የተማሪዎቻችንን ተሞክሮዎች ለማበልፀግ በት/ቤቶቻችን ለሚሰሩ በጎ-ፈቃደኞች ከፍ ያለ አክብሮት አለው። እንደማህበረሰብ፣ ተማሪዎቻችን የሚያድጉበት ሰላማዊ፣ አካባቢዎች መፍጠር የጋራ ሀላፊነታችን መሆኑን እንገነዘባለን። ለእነዚህ አዘውትረው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች (FAQs) የሚመለሱ መልሶች ለበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና እና የወደ ኋላ ታሪክ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ለማጣራት ነው።

የጎብኚ አስተዳደር ስርዓት፦

ጥ1፦ ጎብኝዎች )በጎ-ፈቃደኞችን ጨምሮ)፣ ት/ቤት እንደደረሱ ምን ማድረግ አለባቸው?

መ1፦ በታወቁ የትምህርት ሰዓቶች፣ ሁሉም ጎብኝዎች፣ )በጎ-ፈቃደኞችን ጨምሮ)፣ በMCPS Visitor Management System/የጎብኚ አስተዳደር ስርዓት (VMS) በመጠቀም ት/ቤት ውስጥ ሲገቡ መፈረም አለባቸው።

ጥ2፦ **Visitor Management System(VMS)** የጎብኚ አስተዳደር ስርአት ምንድን ነው?

መ2፦ VMS ከስቴቱ የፆታ/የወሲብ ጥቃት ፈጻሚዎች መዝገብ ጋር የጎብኚው/ዋን መንጃ ፈቃድ ወይም ስቴት የሰጠውን/የሰጣትን መታወቂያ ስካን በማድረግ ያስተያያል። VMS በተጨማሪ በት/ቤቱ ህንፃ ሁልጊዜ መደረግ ያለበትን የሚለጠፍ የስም ባጅ ይሰራል።

ለበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና አስፈላጊ ነገሮች፦

ጥ3፦ ሁሉም በጎ-ፈቃደኞች ስለልጅ መጎሳቆልና ቸልተኝነት መለየትና ሪፖርት አቀራረብ በጎ-ፈቃደኞችና የስራ ተቋራጮች መሰልጠን አለባቸው ወይ?

መ3፦ አዎን። ሁሉም በጎ-ፈቃደኞች አዘውትረው ት/ቤቶችንና ተማሪዎችን የሚደግፉ እና በመስክ ጉዞዎች የሚሳተፉ ሁሉ የልጅ መጎሳቆልና ቸልተኝነትን ለይቶ ስለማወቅና ሪፖርት ስለማድረግ የበጎ ፈቃደኛ ስልጠና መፈፀም ይፈለግባቸዋል። ይህ የስልጠና አስፈላጊነት ዘወትር ት/ቤት የሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች ላይ የሚረዱ/የሚሳተፉ የበጎ-ፈቃደኞችን ሁሉ ያካትታል። (Montgomery County Board of Education Policy JHC የልጅ መበደል/ጉስቁልና እና በቸልተኛነት የተተወ፣ እና የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች ደንብ IRB-RA፣በት/ቤቶች የበጎ- ፈቃደኞች

ጥ4፦ ወደዚህ ስልጠና እንዴት መድረስ እችላለሁ?

መ4፦ ይህ ስልጠና በልጅ መጎሳቆልና ቸልተኝነት ድረ-ገፅ ላይ ይገኛል። (www.montgomeryschoolsmd.org/childabuseandneglect)። Internet Explorer እና Chrome የሚደገፉ የኢንተርኔት መዳሰሻዎች/browsers ናቸው።

ጥ5፦ ለት/ቤቶች ድጋፍ የሚሰጥ ሁሉም የስልጠናውን ግዴታ መፈፀም አለበት ወይ?

መ5፦ ሁሉንም የማህበረሰብ አባሎች በዚህ አስፈላጊ፣ አስተማሪ ስልጠና እንዲሳተፉ የምናበረታታ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት ት/ቤቶችን አዘውትረው የሚደግፉ ግለሰቦችን ብቻ ስለ ልጅ መጎሳቆልና ቸልተኝነት ስልጠና እንዲፈፅሙ እንጠይቃለን። ቢሆንም፣ ይህ ግዴታ በት/ቤት ሰራተኛ አባሎች ቁጥጥር በትላልቅ ዝግጅቶች ላይ ድጋፍ የሚያደርጉ ወይም ለአንድ ወቅት ድርጊቶች በሚያግዙ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም። ከዚህ በታች የበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና መፈፀም የማይጠይቁ እንቅስቃሴዎች ናሙናዎች ተጠቅሰዋል (የተሟላ ዝርዝር አይደለም)፦

- የMCPS ሰራተኛ የሚቆጣጠራቸው በመማርያ ክፍሎች እንግዳ አንባቢዎችና ተናጋሪዎች፤
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት-የኮሌጅ መልማዮችና በጎፈቃደኞች በምልመላ ስራ ላይ ሲሆኑ እና በኮሌጅ በዓላት ጊዜ፣/college fairs
- ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ሌሎች ዘመዶች አንድን በአል ወይም (ለምሳሌ፣ የሰልፍ-ትርኢት) የሚመለከቱ ወይም የሚደግፉ ወይም በመማርያ ክፍል ፓርቲ የሚያግዙ፣
- ወላጆች/አሳዳጊዎች በታላቅ ዝግጅቶች በልዩ ፈቃድ/ቅናሽ የተሰጣቸው በሽያጮችና በቲኬት ጎጆዎች የሚሰሩ።

በጎ-ፈቃደኞች እንዴት አድርገው ነው ስልጠና የሚቀበሉት?

ጥ6፦ መቼ ነው የበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና መስመር ላይ የሚገኘው?

መ6፦ የበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና ሞድዩል ድረ-ገጽ ላይ በ www.montgomeryschoolsmd.org/childabuseandneglect ይገኛል።

ጥ7፡- የMCPSን ስልጠና በ2016-2017 የትምህርት አመት ፈፅሜ ከሆነ፣ በ2017-2018 የትምህርት አመት እንደገና ማድረግ አለብኝ ወይ?

መ7፡- አይደለም። የMCPS መረጃዎች ላይ አንድ ግለሰብ የMCPSን ስልጠና ባለፈው አመት መጨረሱን ካንፀባረቀ፣ ግለሰቡ/ቧ ተጨማሪ ስልጠና መውሰድ የለበትም/የለባትም። ስልጠናው መወሰድ ያለበት በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ/በየሦስት ዓመቱ ነው። የበጎ-ፈቃደኛነት ስልጠና በ ... ተወስዶ ከሆነ፡-
2016-2017 በ 2020-2021 መታደስ አለበት
2017-2018 በ 2020-2021 መታደስ አለበት
2018-2019 በ 2021-2022 መታደስ አለበት

ጥ8፡- ሁሉም በጎ-ፈቃደኞች በድረ-ገጽ ላይ የስልጠና ሞዲዩሉን መፈፀም አለባቸው ወይ?

መ8፡- ሁሉም በጎ-ፈቃደኞች ግዴታው መፈፀሙን የኤሌክትሮኒክስ ማረጋገጫ ለመቀበል በChild Abuse and Neglect ድረ-ገጽ ላይ የሚገኘውን የስልጠና ሞድዩል እንዲፈፅሙ ይበረታታሉ። www.montgomeryschoolsmd.org/childabuseandneglect
ት/ቤቶች የድረ-ገጽ ላይ ሞድዩሉን ለግል ወይም ለአነስተኛ ቡድን የስልጠና ክፍለ ጊዜዎች ለበጎ-ፈቃደኞቻቸው ለመስጠት የመጠቀም አማራጭ አላቸው፣ በተለይም የቋንቋ ትርጉም መገልገያዎች ሲያስፈልጋቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች በመገልገያዎች ምክንያት በት/ቤታቸው ከመሳተፍ አይከለከሉም። ት/ቤቶች ስልጠናዎችን ከሰጡ፣ ት/ቤቱ የተሳታፊው(ዋ)ን ስም እና የመገናኛ መረጃ የመሰብሰብ እናም ወደ በጎ-አድራጊ ስልጠና የውሂብ ጎታ ለማስገባት ዝርዝሩን ወደ Office of Student and Family Support and Engagement/የተማሪና የቤተሰብ ድጋፍና ተሳትፎ ፅ/ቤት (OSFSE) በOSFSE@mcpsmd.org ኢሜይል ማድረግ/መላክ አለበት።

ጥ9፡- ስልጠናውን ለመፈፀም አካለስንክልና ላላቸው መገልገያ ካስፈለገኝስ?

መ9፡- ካስፈለገ ከOSFSE ጋር በመመካከር ርእሰ መምህራንና የት/ቤት ሰራተኞች እንዳስፈላጊነቱ ግለሰቦችን በት/ቤታቸው ውስጥ ማስተናገድ አለባቸው።

ጥ10፡- ድረ-ገጽ ላይ ያለው ስልጠና በበርካታ ቋንቋዎች ይቀርባል ወይ?

መ10፡- አዎን። የመስመር ላይ ስልጠናው በአማርኛ፣ ቻይኒዝ፣ ኮርያን፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ እና ቪየትናሚኛ ይገኛል።

ጥ11፡- በጎ-ፈቃደኞች ስልጠናውን መፈፀማቸውን እንዴት አድርገን እናውቃለን?

መ11፡- በጎ-ፈቃደኞች ስልጠና በፈፀሙ ቁጥር፣ መሳተፋቸውን በMCPS ስለሚመዘገብ ዱካ በመከታተል/ማወቅ ይቻላል።

ጥ12፡- በጎ-ፈቃደኞች አንዴ ከሰለጠኑ በኋላ፣ ከተማሪዎች ጋር መስራት ይችላሉ ወይ?

መ12፡- አዎን፣ በጎ-ፈቃደኞች ት/ቤት ባስቀመጣቸው የተለያዩ መንገዶች ት/ቤቱን መደገፍ ይችላሉ።

ጥ13፡- ከልጃቸው ጋር ምሳ የሚበሉ ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጅ መጎሳቆል - ቸልተኝነት ስልጠና መፈፀም አለባቸው ወይ?

መ13፡- አይደለም። ወላጆች/አሳዳጊዎች በካፌቴርያ ከልጆቻቸው ጋር ምሳ የሚበሉ መደበኛ በጎ-ፈቃደኞች ተብለው አይታሰቡም።

ጥ14፡- ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪዎች ከትም/ በኋላ ወደየቤታቸው በሚሰናበቱበት ጊዜ ወይም በእረፍት ሠዓት እርዳታ የሚሰጡ ከሆነ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል ወይ?

መ14፡- አዎን። በት/ቤት ወይም በት/ቤት ስፖንሰር በተደረጉ እንቅስቃሴዎች ከተማሪዎች ጋር በየጊዜው የሚሰሩ ወላጆች/አሳዳጊዎች በት/ቤት በጎ-ፈቃደኛ ከመሆናቸው በፊት ድረ-ገጽ ላይ ስልጠና መፈፀም አለባቸው።

ጥ15፡- በት/ቤት የሚያግዙ የMCPS ተማሪዎች የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ስልጠና መፈፀም አለባቸው ወይ?

መ15፡- አይደለም። በበጎ-ፈቃደኝነት ት/ቤቶችን የሚረዱ የMCPS ተማሪዎችን ምን ጊዜም የMCPS ሰራተኛ ሊቆጣጠራቸው ያስፈልጋል።

ጥ16፡- ተማሪ መምህራንና ተለማማጅ/ኢንተርን በጎ-ፈቃደኛ ስለ ልጅ መጎሳቆልና ቸልተኝነት ሞድዩል መፈፀም አለባቸው ወይ?

መ16፡- አዎን። ተማሪ መምህራንና ተለማማጆች/ኢንተርን የግዴታ ስለ ልጅ መጎሳቆልና ቸልተኝነት ስልጠና መፈፀም አለባቸው።

የጣት አሻራና የኋላ ታሪክ ማጣራት/**Background Check** አስፈላጊነት/ግዴታዎች:-

**ጥ17**:- ለበጎ-ፈቃደኞች የቀድሞ ታሪክ ማጣራት/**background check** ግዴታዎች ምን ምን ናቸው?

**መ17**:- በሚከተሉት ፈርጆች የበጎ-ፈቃደኛ አገልጋዮች የጣት አሻራና ያለፈ ታሪክ ማጣርያ/background checks የመፈፀም ግዴታ አለባቸው:-

- በጎ-ፈቃደኛ አሰልጣኞች፣
- ለ6ኛ ክፍል የአካባቢ ትምህርት ከመማሪያ ክፍል ውጭ የሚሰጥ ትምህርት/Outdoor Environmental Education ፕሮግራሞች የሌሊት አጃቢዎች/chaperones፣
- በሌሊት የመስክ ጉዞዎች በጎ-ፈቃደኞች፣ እና
- ለረዥም ቀን ጉዞ የበጎ ፈቃድኞች የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት ማጽደቅ ያስፈልጋል። (ለምሳሌ:- የጉዞ መነሻ ሠዓት በ MCPS ሥራ የሚጀመርበት ሠዓት እና/ወይም የመመለሻው ሠዓት ከ7:00 p.m በኋላ ከሆነ)

በስራ ላይ የሚገኙ የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ሕግ አስከባሪዎች በሥራ አቀጣጠር ምክንያት ያለፈ የወንጀል ማጣሪያ ያሚሉ እናም ከMCPS የበፊት ጥናት/ማረጋገጫ አይመለከታቸውም። ቢሆንም፣ ከሕግ አስከባሪ ወኪል ድርጅታቸው ከጣት አሻራ ግዴታ ነፃ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ኦፊሲየላዊ የመመርያ/ መታወቂያ ቅጂ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ሌሎች ለሥራ የጣት አሻራ የሰጡ በሙሉ (ዋይትሃውስ፣ የመንግሥት ኤጀንሲ፣ ወ.ዘ.ተ) በ MCPS አማካኝነት የጣት አሻራ መስጠት አለባቸው ወይም በአሜሪካን አይደንቲቲ ሶሎሽንስ (AIS) (ያለፈውንና የወደፊት የወንጀል እንቅስቃሴዎችን/ሁኔታዎችን) ከባለስልጣናት የ MCPS መሣሪያ ለማግኘት እንዲቻል።

**ጥ18**:- በጎ-ፈቃደኞች ለአለፈ ታርክ ማጣራት/**background checks** የት መሄድ አለባቸው ውጤት ለማግኘትስ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?

**መ18**:- የጣት አሻራና ያለፈ ታሪክ ማጣራት/background checks በሚከተሉት ቦታዎች <u>በቀጠሮ ሊገኙ ይችላሉ:-</u>

- The Office of Human Resources Development/የሰብአዊ ኃይል እድገት ጽ/ቤት (OHRD)፣ የሚገኘውም በ45 West Gude Drive, Rockville, Maryland 20850።
- American Identity Solutions/የአሜሪካ ማንነት መፍትሄ (AIS)፣ የሚገኘውም:-
  - 6701 Democracy Boulevard, Suite 110, Bethesda, Maryland 20817
  - 12501 Prosperity Drive, Suite 200, Silver Spring, Maryland 20904
  - 7361 Calhoun Place, Rockville, Maryland 20855
- የአለፈ ታሪክ የማጣራት ሂደት ለመጨረስ አራት ሳምንቶች አካባቢ ይወስዳል።

**ጥ19**:- የአለፈ ታሪክ ማጣሪያ ለመፈፀም በጎ-ፈቃደኞችን ማን ይከፍላቸዋል?

**ም19**:-

- የአለፈ ታሪክ ለማጣራት የሚከፈል ዋጋ መሸፈን የበጎፈቃደኛ ሀላፊነት ነው። በጎ ፈቃደኞች የሚከፍሉት በOHRD $54፤ በAIS ደግሞ $59 ነው። እያንዳዱ ጉዳይ እየታየ፣ ወጪዎቹ የሚሸፈኑበትን መንገድ ት/ቤቶች ከበጎ-ፈቃደኞች ጋር ሊነጋገሩ ይችላሉ።
- ከቤት ውጭ ትምህርት የሌሊት አጃቢዎች/chaperones የጣት አሻራ በOHRD በኩል ከተፈፀመ ለአለፈ ታሪክ ማጣራት/background checks ወጪ አይኖራቸውም። ነገር ግን፣ AIS የሚጠቀሙ በአጃቢነት የሚሰሩ/chaperones $20.00 ይከፍላሉ።
- በጎ-ፈቃደኛ አሰልጣኞች፣ በአትሌቲክ መምርያ በኩል እንደተዘጋጀው፣ የአለፈ ታሪክ ለማጣራት/background checks መክፈል ይቀጥላሉ።

**ጥ20**:- የ**MCPS** የአለፈ ታሪክ ማጣራት/**background checks** ባለፈው አመት ከፈፀምኩ ሌላ የአለፈ ታሪክ ማጣራት ማድረግ አለብኝ ወይ?

**መ20**:- አንድ ወላጅ/አሳዳጊ/የማህበረሰብ አባል አስቀድሞ የMCPS የአለፈ ታሪክ ማጣራት ሂደት/background checks በ2016-2017 የትምህርት አመት ከፈፀመ፣ ያ ግለሰብ ሂደቱን እንደገና በ2017-2018 የትምህርት አመት መፈፀም የለበትም።

**ጥ21፡-** የአንድ ት/ቤት **Parent Teacher (Student) Association (PTA/PTSA)** የወላጅ/ተማሪ ማህበር ከትምህርት ውጭ የሚከናወን እንቅስቃሴ፣ እድገት ፕሮግራም፣ ወይም ሌላ ፕሮግራም ስፖንሰር ካደረጉ፣ የጣት አሻራ/የአለፈ ታሪክ ማጣራት/**background checks** በሚመለከት በ**MCPS** የስራ ተቋራጮች ላይ ያለው ግዴታ በአቅራቢዎቹም ላይ ይሰራል ወይ?

**መ21፡-** የጣት አሻራ እና የአለፈ ታሪክ ማጣራት/background checks ተፈላጊነታቸው በት/ቤት ስፖንሰር በሆኑ ድርጊቶች ላይ ብቻ ነው።

- ከትምህርት-ውጭ ፕሮግራሙ በMCPS ገንዘብ ከተሰጠው ወይም ስፖንሰርድ ከሆነ ወይም MCPS የኮንትራቱ አካል ከሆነ (ይህም ማለት፣ የርእሰ መምህሩ/ሯ ፊርማ ኮንትራቱ ላይ ካለ)፣ ስልጠና ያስፈልጋል እናም የትምህርት-ውጭ ፕሮግራሙ አቅራቢዎች ቀጥተኛ፣ ቁጥጥር የሌለው መዳረሻ ወደ MCPS ተማሪዎች በ MCPS አገልግሎት መስጫ መዳረሻ ካለው የአለፈ ታሪክ ማጣራት/ background checks ይፈለጋል።
- ኮንትራቱ በት/ቤት ስፖንሶርድ ካልሆነ እና ብቸኛ ስፖንሰር PTA/PTSA ወይም ሌላ ድርጅት ከሆነ፣ ወይም Interagency Coordinating Board/የወኪል ድርጅቶች አስተባባሪ ቦርድ (ICB) ብቻ ከተደራጀ፣ MCPS የአለፈ ታሪክ ማጣራት/background checks ወይም ስልጠና አይጠይቅም። ቢሆንም፣ PTA/PTSA ወይም ICB ለስራ ተቋራጮቻቸው ተጨማሪ ግዴታዎች ሊኖሯቸው ይችላል።

**ጥ22፡-** በበጎ-ፈቃደኛነት ለማገልገል ዝንባሌና ፍላጎት ያላቸው ፈቃድ ማግኘታቸውንና አለማግኘታቸውን ማን ይነግራቸዋል?

**መ22፡-** ለበጎ-ፈቃደኛነት ተዘጋጅተው የሚጠባበቁት የአለፈ ታሪክ ማጣሪያ/background check ውጤቶችን በፖስታ ያገኛሉ። የMCPS OHRD አንድ በአንድ ትንተና ያካሂዳል እና ወድያውኑ ስለ ፆታዊ ጥቃቶች/በደሎች፣ የልጅ ፆታዊ ማጎሳቆል በደሎች፣ እና የሁከት ወንጀል፣እንዲሁም የረብሻ ወንጀሎችን እና የሆኑ በደሎችን፣ የእፆችና ሌሎች የተከለከሉ ነገሮችን ማሰራጨት፣ ወይም ሌላ የወንጀል መረጃ የMCPS ተማሪዎችን ደህንነትና ፀጥታ የሚነኩ መረጃዎችን ይከታተላል። OHRD ለበጎ-ፈቃደኛነት ታጭተው የአለፈ ታሪክ ሲጣራ የተገኙ የወንጀል ዝርዝሮችን በሚመለከት በት/ቤት ከሚገኙ ሰራተኛ አባሎች ጋር አይጋራም።

**ጥ23፡-** ስለ በጎ-ፈቃደኛ ስልጠናና የአለፈ ታሪክ ማጣራት/**background checks** በሚመለከት ጥያቄዎች ካሉኝ ማንን መጠየቅ አለብኝ?

**መ23፡-** ስል በጎ-ፈቃደኛ ግዴታዎች የሆኑ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካለዎት ት/ቤትዎን ይጠይቁ። በተጨማሪ፣ በት/ቤት ደረጃ ያልተፈቱ ቅሬታዎች ወደ Dr. Jonathan T. Brice/ጆናኣታን ቲ ብራይስ ረዳት የበላይ ተቆጣጣሪ፣ OSFSE፣ በ240-453-2426 መመራት ይችላሉ።

**ጥ24፡-** እነዚህ መሟላት የሚገባቸው ነገሮች/**requirements** በ**MCPS** የሥራ ጣቢያዎች በሚሠሩ የሞንጎመሪ ኮሌጅ ሠራተኞች ተፈፃሚ የሚሆኑት እንዴት ነው?

**መ24፡-** በ ሁለትዮሻዊነት ፕሮግራም (dual enrollment program) ገብተው የሚሠሩ የሞንጎመሪ ኮሌጅ ሠራተኞች የጣት አሻራን ጨምሮ የወንጀል ማጣራት ሂደት ጨርሰው/አልፈው ነው የሚቀጠሩት። ት/ቤቶች በሚገኙበት ጊዜ ከሞንጎመሪ ኮሌጅ የሚሰጣቸው ተለጣፊ መታወቂያ/badge በሚታይ ዓይነት ማድረግ ወይም ከራሳቸው ጋር መያዝ አለባቸው።

**ጥ25፡-** እነዚህ መሟላት ያለባቸው ነገሮች በሞንጎመሪ የመንግስት ሠራተኞችስ (**MCG**) ላይ እንዴት ነው ተግባራዊ የሚደረጉት?

**መ25፡-** የሞንጎመሪ ካውንቲ የማንግስት /MCG ሠራተኞች፤ ለምሳሌ፡- ነርሶች እና የጤና ክፍል ቴክኒሻኖች፣ በቅጥር አፈጻጸም ወቅት የጣት አሻራን ጨምሮ የወንጀል ማጣራት ሂደት ያካሄዳሉ። በት/ቤቶች ውስጥ በሚገኙበት ጊዜ በMCG-ወጪ የተደረገ የመታወቂያ ተለጣፊያቸውን/badge የሚታይ ማድረግ ወይም ከራሳቸው ጋር መያዝ አለባቸው። MCPS የወንጀል ማጣራት ሂደት ላጠናቀቁ ከትምህርት ፕሮግራሞች ጋር ለሚገናኙ የካውንቲ ሠራተኞች በሙሉ የመታወቂያ ካርድ ይሰጣቸዋል።